# የኢኮኖሚ እድገት ትርክቶችን አውድ ማስተካከልና ችግር ያለባቸውን መረጃዎች መፈተሽ - የኢትዮጲያ ኢኮኖሚ በጊዜ ሂደት ውስጥ (ከ 1999 እስከ 2017)

ሎገን ኮክረን[1, 2, *] እና የሺጥላ ወ. በቀለ[2, 3]

[1] Global and International Studies, Carleton University, Ottawa, ON K1S 5B6, Canada

[2] Institute of Policy and Development Research, Hawassa University, Hawassa 1558, Ethiopia; yeshtila@yahoo.com

[3] Department of International Environment and Development Studies, Norwegian University of Life and Sciences, Ås 1430, Norway

[*] የጸሐፊው አድራሻ፡- logan.cochrane@gmail.com; Tel.: +1-613-520-2600 (ext. 5066)

Received: 9 September 2018; Accepted: 29 November 2018; Published: 3 December 2018

**እጥርጥር፡** በኢትዮጲያ ስላለው የኢኮኖሚ እድገት የተለመዱ ትርክቶች አሉ፡፡ አራት የተለመዱ ትርክቶችን እንፈትሻለን፤ እነርሱም፡- (1) ኢኮኖሚው ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ሽግግር እያደረገ ነው፣ (2) ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገቱ ፈጣንና ዘላቂ እየሆነ ነው፣ (3) የኢትዮጲያ ኢኮኖሚ በአብላጫው ግብርና ላይ የተመሰረተ ነው፣ እና (4) በተለይም ከቻይና ጋር ባለው የብድር ሁኔታ ምክንያት በሀገሪቱ ላይ ያጠላ አስጊ የብድር ችግር አለ፡፡ የእነዚህን ትርክቶች እውነተኛነት ለማሳማን የሚቀርቡት አብዛኞዎቹ ማስረጃዎች የአንድ ዓመት ወይም ውሱን የሆኑ የመረጃ ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ትርክቶች በረጅም ጊዜ ውስጥ ያላቸውን ሁኔታ እንመረምራለን፤ ባሉት የማክሮ ኢኮኖሚ መረጃዎች መሰረትም ያላቸውን ድጋፍ እንመለከታለን፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ጥራት እና ወጥነት ችግር አጋጥሞናል፡፡ ይህ ጽሁፍ በ 1999 እና 2017 መካከል ማግኘት የተቻለውን መረጃ በመመልከት በኢትዮጲያ ኢኮኖሚ ላይ በተለምዶ የሚሰጡ አስተያየቶች አንዳንድ ጊዜ ትክክል እንደሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜ ጉድለት እንዳለባቸውና በሌላ ጊዜ ደግሞ ትክክል እንዳልሆኑ ይደመድማል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ጠቅላላ፣ የአንድ ዓመት፣ እና ውሱን መረጃዎችን ተጠቅሞ አጠቃላይ አስተያየቶችን ከመስጠት ይልቅ በመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችና የመረጃ ስብስቦች ላይ መሰረት መደረግ እንዳለበት አጥብቀን እናሳስባለን፡፡

**ቁልፍ ቃላት፡** ኢትዮጲያ፣ ኢኮኖሚ፣ እድገት፣ ንግድ፣ ውጪ ንግድ፣ ገቢ ንግድ፣ ብድር

**JEL Classification:** A1; E6; O4; Y1

## 1. መግቢያ

የኢትዮጲያን አኮኖሚ በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚነሱና የገነኑ ትርክቶች አሉ፤ ነገር ግን ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የተሰሩ ምርመራዎች ጥቂት ናቸው፡፡ የኢትዮጲያ መንግሥት ለረጅም ጊዜ ሲያስተዋውቅ የቆየው የኢትዮጲያ ገጽታ "ኢትዮጲያ በከፍታ ጎዳና" የሚሰኝ ነው፣ በምርምርና በትምህርት ዓለሙ ያሉት ደግሞ "የአፍሪካ ቻይና" (Cowen 2018) ብለው ሰይመዋታል፣ ዓለምአቀፍ ተቋማት ኢትዮጲያ በዓለማችን ከፍተኛ ፍጥነት ከሚያሳዩ ኢኮኖሚዎች አንዷ እንደሆነች ይናገራሉ (World Bank 2018)፣ ጋዜጠኞች ደግሞ ኢትዮጲያ ያለችበትን ወቅት ተዓምራዊ ሽግግር በማለት ያደንቁታል (Kopf 2017)፡፡ የእነዚህ ትርክቶች አንደኛው ችግር በማደግ ላይ ያለው የኢኮኖሚ ጥቅም ክፍፍል ላይ ያለው ጥያቄ ነው፤ ይኸውም የኢኮኖሚ እድገቱ ማንን ይጠቅማል፣ እድገቱስ የመጣው በማን

ጫንቃ ላይ ነው የሚሉትን ጥያቄዎች ያጠቃልላል (Haylemariam 2017)፡፡ ይህ አይነቱ ሂሳዊ አካሄድ የመረጃን ትክክለኝነት ጥየቄ ውስጥ ከማስገባቱም በተጨማሪ ከአብዛኛው ኢትዮጲያዊ የእለት ተእለት የኑሮ ሁኔታ አንጻር የዚህ ጠቅላላ ትርክትን አግባብነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባል፡፡ እንዲህ አይነት ጠቅላላ አስተያየቶች እየጨመሩ የመጡ አለ-እኩልነቶች፣ ሥር የሰደደ ድህነት፣ እና በኢኮኖሚ ለውጥ ምክንያት የመጡ አዳዲስ ተጋላጭነቶች እንዲደበቁ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ መጠየቅ ያለባቸውና ሂስ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ በቅርብ ጊዜ አየወጡ ያሉ ጥናቶች እየጨመረ የመጣውን የአለ-እኩልነት መገለጫዎችና ችግሮች ትኩረት እየሰጡት ነው (ለምሳሌ፡- Cochrane and Rao 2018; Rammelt et al. 2017; UNDP 2015)፡፡ የዚህ ጽሁፍ ዓላማ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ የተለመዱት ትርክቶች በሚገኘው መረጃ መደገፍ መቻላቸውን ለመመርመር የመጀመሪያ መረጃ ስብስብን እንጠቀማለን፡፡ በዚህ ሂደት ውሰጥ ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎችን በማግኘታችን ምክንያት አንዳንድ ትርክቶች በመረጃ ቢደገፉም እንኳ ትክክል ላይሆኑ እንደሚችሉ እንገምታለን፤ በመሆኑም መረጃዎቹ ውስጣዊ ወጥነት እንዳላቸው እንፈትሻለን፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጲያ መንግሥት ትርክት በራሱ መንግሥት መረጃ መደገፉን እንፈትሻለን፡፡

የኢትዮጲያ ማክሮ ኢኮኖሚ ከፍተኛ የሆነና ቀጣይነት ያለው እድገት እየስመዘገበ ነው የሚለው በጣም የተለመደው ትርክት ቢሆንም ስለ ኢትዮጲያ ማክሮ ኢኮኖሚ ታሪክ የሚነገረው የተለመደ ትርክት ግን ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ኢትዮጲያ በኢኮኖም ሽግግር ላይ እንደሆነችና በተለይም በግብርና ላይ ከመመስረት በማለፍ ኢኮኖሚው ዘርፉን እየለወጠና በስፋት ወደ አምራችነት እየተቀየረ ነው የሚለው ደግሞ ሌላኛው ትርክት ነው፡፡ ሦስተኘው ትርክት የግብርናው ዘርፍ በኢኮኖሚው ላይ ስለሚጫወተው ወሳኝ ሚና ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መሰማት የተጀመረው ትርክት ደግሞ በሀገሪቱ አስጊ የብድር ችግር እየተከሰተ እንደሆነና በተለይም ከቻይና ጋር ያለው የብድር ሁኔታ አሳሳቢ አንደሆነ የሚያስረዳው ነው፡፡ በዚህም ጽሁፍ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን በመመልከትና በጊዜ ሂደት ውስጥ እነዚህ ትርክቶች ያላቸውን ሁኔታ ለመፈተሸ የረጅም ጊዜ መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡ የኢኮኖሚ እድገትን በተመለከተ ሁለት የመረጃ ስብስቦችን እንመለከታለን ፣ የተለያዩ ዘርፎች በኢኮኖሚው ላይ ያላቸውን ድርሻ የሚያሳዩ መረጃዎችን እንመለከታለን፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የወጪና የገቢ ንግድ ያላቸውን ሁኔታ እንመረምራለን፣ በተጨማሪም የሀገሪቱን የብድር መጠን እንፈትሻለን፡፡ ሰፊውን የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ የሚፈትሹ የረጅም ጊዜ ዳሰሳዎች ጥቂት ሲሆኑ (Geda 2011) እኛ እስከምናውቀው ድረስ የመረጃ ስብስብ የንጽጽር ጥናቶች ወይም ከአንድ ምንጭ የተገኘን መረጃ ወጥነት ለመፈተሽ  የተደረጉ ምንም አይነት ጥናቶች የሉም፡፡ የረጅም ጊዜ መረጃዎችን የሚፈትሹ ጥናቶች ቢኖሩም ትኩረታቸው እንደ 'የመንግሥት ወጪ' (Menyah and Wolde-Rufael 2013) ወይም 'የውጪ ንግድ' (Allaro 2012) በመሳሰሉት ልዩ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ትርክቶች ላይ እና እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ መረጃዎች ላይ ጥልቅ ፍተሻ በማድረጋችንና ይህንን ጉዳይ አጉልተን በማሳየታችን ወደፊት መሰል ጥናቶች እንዲሰሩ አበረታተናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

እነዚህን ትርክቶች፣ የእነርሱን ትክክለኝነት የሚሞግቱትንም ሆነ ስህተት ለመሆናቸው ማስረጃ የሚያቀርቡትን መመርመር ወሳኝ ነው፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጲያ መንግሥት አገሪቱ እያሳየችው ነው ብሎ የሚያቀርበው አጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) እንደ ዓለም ባንክ ካሉ ሦስተኛ ወገኖች ከሚያቀርቡት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ለዚህ ለተለመደ አነጋገር (ለምሳሌ ፡- Mandefro 2016; Mandefro and Jerven 2015) ማመሳከሪያ ተደርገው የሚቀርቡት ነጠላ የመረጃ ነጥቦች ወይም የተወሰኑ ዓመታት መረጃዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በታች የአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) ጉዳይ ጋር በተገናኘ እንደምናሳየው ነጠላ የመረጃ ነጥቦችን የመመረጥ ችግሩ እንዲህ አይነት መረጃዎች በጊዜ ሂደት ያለውን ሁኔታ ስለማይወክሉ ነው፡፡ ትርክቶችን የሚፈጥሩት ደግሞ ጋዜጠኞች እና  ተመራማሪዎች ብቻ አይደሉም፡፡ የኢትዮጲያ መንግሥትም በሰፋፊ የጽነሰ-ሐሳብ ማዕቀፍ ውስጥ በማስገባት የራሱን ትርክት ይፈጥራል፤ ለምሳሌ መንግሥት የትራንሰፎርሜሽን ትርክትን ሲያቀርብ ሰፊ በሆነው የ "ልማታዊ መንግሥት" ጽንሰ-ሐሳብ ውስጥ በመከተት ወይም ከእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ዓላማዎች ጋር በማገናኘት ነው፡፡ በኢትዮጲያ ያለው የልማታዊ መንግሥት መገለጫዎች በሌሎች ቦታዎች የሚስተዋለውን የልማታዊ መንግሥትት ባሕርያት ያንጸባርቃል፤ እነዚህም ጣልቃ ገብነተ ያለው፣ ጠንካራ፣ እና ራዕይ-ተኮር (Dejene and Cochrane 2018) መሆን ናቸው፡፡ የዚህ አስተሳሰብ ቀራጺ የሆነው የቀድሞው

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ስኬታማ፣ አስፈላጊና፣ ለረጅም ጊዜያት የሚዘልቁ ፖሊሲዎችን ለመፍጠር የልማታዊ መንግሥት እሳቤ ወሳኝ እንደሆነ እምነት ነበረው (Clapham 2017; Zenawi 2012, n.d.)፡፡ የኢኮኖሚ ሽግግርን ከማምጣትና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ከማስመዝገብ ጋር የተገናኙትና በዚህም ጽሁፍ የሚመረመሩት የአንዳንዶቹ ትርክቶች መሰረት ይኸው የልማታዊ መንግሥት እሳቤ ሲሆን በዚህም አካሄድ እነዚህን ትርክቶች ለማሳካት እንደሚቻል ይታሰባል፡፡ እነዚህም ትርክቶች የልማትና የትራንስፎርሜሽን እቅዱ ዓላማዎች ሆነው ተጽፈዋል፡፡ የኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት ያመጣቸው አዎንታዊ ለውጦች ሲኖሩ አንዳንዶቹም በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ቀርበዋል፤ ነገር ግን እነዚህ ለውጦች በተለይም ከሙብትና ከነጻነት አንጻር ከፍተኛ ዋጋን አስከፍለዋል (Dejene and Cochrane 2018)፡፡ ይህ ጽሁፍ አራት የማክሮ ኢኮኖሚ ትርክቶች ላይ ጥልቅ ግምገማ ያደርጋል፤ የኢትዮጲያ ልማታዊ መንግሥት እሳቤንም ጨምሮ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶችም መሰረት ይጥላል፡፡

ከኢትዮጲያ መንግሥት የሚገኙትን መረጃዎች በምንጠቀምበት ወቅት እነዚህ መረጃዎች ሁልጊዜ ትክክለኛ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ በዚህ ግምገማ ወቅት እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ብዙ መረጃዎችን አግኝተናል፤ ከዚህ ጥናት በተጨማሪ ሌሎች ጥናቶችም በመንግሥት የሚዘጋጀው ስታቲስቲክስ ችግር እንዳለበት ያስረዳሉ (Cochrane and Bekele 2018; IMF 2013)፡፡ ይህ አይነቱ ችግር በመንግሥት የስታቲስቲክስ ተቋማትና በአጠቃላይ በደቡባዊው የዓለም ክፍል የሚስተዋል የመረጃ እና የመረጃ ጥራት ችግር ሲሆን ይህ ግምገማም የዚህ ሰፊ ክፍል አካል ነው (Carletto et al. 2015; Jerven 2013; Sandefur and Glassman 2015; Sundaram 2016)፡፡ ይህ ጽሁፍ በኢትዮጲያ ኢኮኖሚ ላይ በተለምዶ የሚሰጡ አስተያየቶች አንዳንድ ጊዜ ትክክል እንደሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜ ጉድለት እንዳለባቸውና በሌላ ጊዜ ደግሞ ትክክል እንዳልሆኑ ይደመድማል፡፡

## 2. የጥናት ስልት

ትርክቶቹን ለመፈተሽ የተጠቀምነው የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ስብስቦችን እና የረጅም ጊዜያትን መረጃ ነው፡፡ ኢኮኖሚውን በተመለከተ የተጠቀምናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች የተወሰዱት ከኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ አመታዊ ሪፖርት፣ ከኢትዮጲያ ቀረጥ እና ገቢዎች ባለሥልጣን ሪፖርቶች፣ እና ከንግድ ሚኒስቴር መረጃዎች ላይ ነው፡፡ መረጃዎቹን ለማነጻጸርና ለማሟላትም ከዓለም ባንክ እና ከምጣኔ-ሐብት ውስብስብነት ምልከታ ማዕከል (Observatory of Economic Complexity)የተወሰዱ ሌሎች መረጃዎችም አሉ፡፡

ከእነዚህ መረጃዎች አንዳንዶቹ ችግር ነበረባቸው፡፡ በተለይም የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክን እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ መጠቀም የራሱ የሆኑ ብዙ ችግሮች አሉት፡፡ በዋናነት የሚጠቀሱት መረጃዎች እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ እያንዳንዱ ዓመታዊ ሪፖርት ያለፉት ዓመታት ንጽጽራዊ እና በየዓውዱ የተቀመጡ መረጃዎች አሉት፤ ነገር ግን በአንድ ሪፖርት የተቀመጠው የአንድ ዓመት የመረጃ ዝርዝር ከሌላኛው ሪፖርት ሊለይ ይችላል፡፡ በ2004/05 ዓመታዊ ሪፖርት ላይ በ2000/01 የግብርና ዘርፉ ከአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) 45% እንደያዘ ሲገለጽ በ 2005/06 ዓመታዊ ሪፖርት ላይ ግን ይኸው መረጃ 48.4% እንደሆነ ተገልጿል (NBE 2005; 2006; አንዳንድ ምሳሌዎችን በ ሠንጠረዥ 1 ላይ ተመልከቱ)፡፡ የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ዓመታዊ ሕዝባዊ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት የጀመረው በ2004/05 ነው፤ በዚህም ምክንያት ከዚህ ዓመት በፊት ያሉትን መረጃዎች የወሰድነው ከዚህ ዓመት በኋላ ከታተሙ ሪፖርቶች ነው፡፡ ይህ ያስከተለው ችግር መረጃዎቹ ከሪፖርት ሪፖርት ልዩነት የሚያሳዩ መሆናቸው ነው፤ ይህ ከፍተኛ ስልታዊ ችግርን ፈጥሯል፡፡ ከ 2004/05 በፊት ያሉትን መረጃዎች ለማግኘት ቀዳሚ ሆኖ የተገኘውን ሪፖርት ማለትም የ2004/05ቱን ተጠቅመናል፡፡ የአንድ የተወሰነ ዓመት ሪፖርት ካለ ግን እኛም በዚህ ሪፖርት ላይ ያለን መረጃ ተጠቅመናል (በሌላ አባባል ለ 2004/05 መረጃ የ 2004/05 ሪፖርትን ተጠቅመናል)፡፡ ይህ የተጠቀምነው አካሄድ በዘፈቀደ የተደረገ እንደሆነ እናምናለን፤ ነገር ግን ከዚህ ውጪ ያለን አማራጭም እንዲሁ በዘፈቀደ የተደረገ አልያም በመረጃው ላይ ሌላ ማስተካከያ ወይም ስሌት የሚፈልግ ሲሆን ይህ ደግሞ የበለጠ ችግር የሚፈጥር እንደሆነ እናስባለን(ምክንያቱም ይህ አካሄድ ከብሔራዊ ባንክ ሪፖርቶች ውጪ ያሉ መረጃዎች እንዲካተቱ ያደርጋል)፡፡

**ሠንጠረዥ 1.** እርስ በእርስ የሚጋጩ መረጃዎች ምሳሌ፤ ከአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) ግብርናው ያለው ድርሻ በመቶኛ

| Agriculture as % of GDP | 2000/01 | 2001/02 | 2002/03 | 2003/04 |
|---|---|---|---|---|
| 2004/05 Report | 45 | 49 | 44 | 47 |
| 2005/06 Report | 48.4 | 47 | 43 | 45.1 |
| 2006/07 Report | - | 48.9 | 44.6 | 46.7 |
| 2007/08 Report | - | - | 44.6 | 46.7 |
| 2008/09 Report | - | - | 44.9 | 47.0 |

ምንጭ፡- NBE 2005, 2006, 2007, 2008

ከ 2004/05 ቀድመው ያሉና እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ መረጃዎችን ለማስተካከል ምንም ቀላል መንገድ የለም (ዓመታዊ ሪፖርቶች መውጣት የጀመሩት ከዚህ ዓመት ጀምሮ ነው)፡፡ ይህን የበለጠ አስቸጋሪ የሚያደርገው በአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) መሰረት 3% ከፍተኛ የቁጥር ልዩነት መሆኑ ነው፡፡ ይህ አይነት እርስ በእርሱ የሚጋጭ መረጃ የሚስተዋለው ከ2004/05 ዓመት በፊት ባሉት መረጃዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በአዳዲሶቹ ሪፖርቶቹ ላይ ባሉት የቀድሞ ዓመታት መረጃዎችም ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ በ2004/05 ግብርናው በአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) በመቶኛ ያለውን ድርሻ አንደኛው ዓመታዊ ሪፖርት 48% እንደሆነ ሲዘግብ በ2006/07 ዓመታዊ መረጃዎችን ለንጽጽር ያወጣው ሪፖርት ደግሞ የ2004/05 የግብርናው ድርሻ 47% እንደሆነ ይዘግባል፡፡ እነዚህ እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ መረጃዎች በጊዜ ሂደት ውስጥ የመስተካከል አዝማሚያም የላቸውም፤ በቅርብ በወጡ ዓመታዊ ሪፖርቶችም ላይ ችግሮቹ ይታያሉ፡፡ በ2010/11 ዓመታዊ ሪፖርት ላይ ከአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) የግብርናው ድርሻ 41.1% እንደሆነ ሲገለጽ በ2011/12 ሪፖርት ደግሞ ይኸው የ 2010/11 አኃዝ 45.3% እንደሆነ ተዘግቧል፡፡

መሰል ችግሮችም በሌሎች መረጃዎች ላይ ይስተዋላሉ፡፡ በአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) የሚዘገበው አገራዊ የእድገት አኃዝ መረጃም እርስ በእርሱ የሚጋጭና ሰፊ ልዩነቶች ያሉት ነው፡፡ አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ በ2004/05 ሪፖርት መሰረት የዓመቱ አጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) 8.8% እንደሆነ ሲገለጽ በ2011/12 ሪፖርት ግን የ2004/05 መጠን 12.7% ነው (NBE 2005, 2011)፡፡የውጪ ንግድን መረጃም በተመለከተ እርስ በእርሱ የሚጋጩ መረጃዎች ቢኖሩም ከሌሎች የመረጃ ስብስቦች ጋር ሲነጻጸር የዚህ ዘርፍ መረጃ ችግር አነስተኛ ነው(የውጪ ንግድን የተመለከቱ መረጃዎችንም የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ያቀርባል)፡፡ እነዚህን የመረጃ ችግሮች በተመለከተ የተጠቀምነው ሂደት ከላይ የተገለጸው አይነት ነው(ይኸውም የዓመቱን መረጃ የምንወስደው በዚያን ዓመት ከታተመው ሪፖርት ላይ ሲሆን በቀጣይ ዓመታት ከሚወጡ ሪፖርቶች ላይ ባሉ አኃዞች ማስተካከያዎችን አላደረግንም)፡፡

እነዚህ አኃዞች ከሪፖርት ሪፖርት ያላቸው ልዩነት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለማስረዳት ከግምት የዘለለ አስተያየት መስጠት አንችልም፡፡ ነገር ግን እነዚህ አኃዞች ፖለቲካዊ ይዘት ሊኖራቸውና በዚህም ድጋፍ ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ የመዋል አቅም አላቸው፤ በተለይም መንግሥት የሚያራምደውን የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን ትርክት ድጋፍ ለመስጠት እና የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ግቦቹ በመሳካት ሂደት ላይ እንደሆኑ እንደ ማሳያ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሰውንና በ2010/11 ግብርናው በአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠኑ (GDP) ውስጥ ያለውን ድርሻ ብንመለከት 41.1% እንደሆነ በዚሁ ዓመት በታተመው ሪፖርት ተጠቅሷል (NBE 2011) ነገር ግን ይኸው የ 2010/11 አኃዝ በቀጣይ ዓመታት ሪፖርቶች ላይ ለውጥን ሲያሳይ እንመለከታለን፤ ይኸውም 45.3% (NBE 2012, 2013)፣ 44.4% (NBE 2014, 2015)፣ እና 44.7% (NBE 2016) ነው፡፡ በዚህም መሰረት እነዚህ አኃዞች ሪፖርቱ በወጣበት ዓመት ላይ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን እየተካሄደ እንደሆነ እንደማሳይ በመሆን ሊቀርቡ ሲችሉ በተጨማሪም በቀጣይ ዓመታት ደግሞ አኃዞቹን በማስተካከል (በመጨመር) ለንጽጽር እንዲያገለግሉ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ (ይህ ደግሞ ከፍተኛ የለውጥ

መጠን በማሳየት የትራንስፎርሜሽኑን ትርክት ደጋፊ ሆኖ ይቀርባል)፡፡ የመረጃው እርስ በእርሱ መጋጨት ለዚህ አይነት ዓላማ መሆኑን ወይም ስልታዊ ለውጦች ተደርገው እንደሆነ በእርግጠኝነት መናገር አንችልም፡፡ ለውጦቹ ወጥነት ይጎድላቸዋል፤ በመሆኑም የለውጡ ምክንያት ከስልት ጋር የተያያዘ ቢሆን ኖሮ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ያለው ለውጥ ወጥ ይሆን ነበር፡፡ በተጨማሪም አኃዞቹ ለውጥ ያመጡት ታስቦበት በተደረገ ማስተካከያ ቢሆን ኖሮ ይህ ማስተካከያ ከተደረገ በኋላ በወጡት ሪፖርቶች ላይ የቀደሙ ዓመታት መረጃዎች የተወሰነ ወጥነት ይኖራቸው ነበር፤ ነገር ግን መረጃዎቹ ይህንን አይነት አዝማሚያም አያመላክቱም፡፡ በእርግጠኝነት መናገር የምንችለው ነገር ቢኖር መረጃዎቹ እርስ በእርሳቸው እንደሚጋጩና ጥቅም ላይ ሲውሉም በጥንቃቄ ሊሆን እንደሚገባ ነው፡፡ ትክክለኛ አኃዞችንና እነዚህንም ለማግኘት መጠቀም ያሉብንን ሪፖርቶች በተመለከተ የእነዚህ መረጃ ስብስብ ተጠቃሚዎች ሊያዉቁት የሚገባው ነገር ቢኖር ከፍተኛ በሆነ መልኩ ወጥነት እንደሚጎድላቸው ነው፡፡ ከፍተኛ የሆነ ችግር የነበረው የመረጃ ስብስብ ዘርፎች በኢኮኖሚው ላይ ያላቸውን ድርሻ የሚያሳየው ነው፤ ይህንን መረጃ በተመለከተ አንደኛው የጥንቃቄ አካሄድ እንደሆነ የምናስበውና ተጠቃሚዎችን የምናበረታታው እኛ እንዳደረግነው በጊዜ ሂደት ውስጥ ያሉትን ለውጦች የሚያሳዩትን መረጃዎች የያዙ ሠንጠረዦች (ለምሳሌ ሠንጠረዥ 1) ጥናቶች ውስጥ መካተት እንደሌለባቸው ነው፡፡ ነገር ግን ሌሎች አኃዞችን በተመለከተ አባሪ የሆኑ የሠንጠረዥ መረጃዎችን አካተናል፡፡ ይህንን ማድረጋችን ሌሎቹ መረጃዎች ወጥነት እንዳላቸው ለማመልከት ሳይሆን በኢኮኖሚው ውስጥ የየዘርፎቹን ድርሻ የሚያሳዩትንና ከኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ የተገኙት ሪፖርቶች ከሌሎቹ አንጻር ያላቸው የወጥነት ችግር የከፋ መሆኑን ነው፡፡

## 3. ግኝቶች

የኢትዮጲያ ኢኮኖሚ ሽግግር እያደረገ ነውን? የኢትዮጲያ መንግሥት ትርክት የሚጠቁመው ትርጉም ያለው የኢኮኖሚ ሽግግርን እያካሄደ እንደሆነ ነው(MoFED 2014, 2017)፤ እኛም ይህንን የመጀመሪያውን ትርክት ለመፈተሽ እንሞክራለን፡፡ ሁለተኛው የእድገት እና የትራንስፎርሜሽን እቅድ (2015/16 እስከ 2019/20) የኢንዱስትሪው ዘርፍን ማሳደግ ከፍተኛ የትኩረት አቅጣጫው ነው (NPC 2016)፡፡ ይህንን የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማሸጋገር መንግሥት በመላ አገሪቱ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም ላይ ይገኛል፡፡ ኢትዮጲያ የመጀሪያውን የኢንዱስትሪ ዞን በ2008 ላይ በዱከም ስታቋቁም፣ ሁለተኛውን በ2014 በአዲስ አበባ፣ ሦስተኛውን ደግሞ በ2016 በሐዋሳ አቋቁማለች፡፡ በአጠቃላይ 20 የሚሆኑና በሥራ ላይ ወይም በመገንባት ላይ ያሉ ሌሎችም አሉ (ABP 2017)፡፡ በአገሪቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረት (NPC 2016) ኢኮኖሚውን ለማሸጋገር ይህ ቁልፍ ከሆኑ ተግባራት አንዱ ነው፡፡

እንደ የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ መሰረት ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ግብርናው በአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠኑ (GDP) ላይ ያለው ድርሻ መጠነኛ ማሽቆልቆል ሲያሳይ የኢንዱስትሪው እና የአገልግሎት ዘርፎች ደግሞ ጭማሬን አሳይተዋል፡፡ ከዚህ አካሄድ ትንሽ ለየት የሚለው ለውጥ የተገኘው መረጃ ባገኘንበት በመጨረሻው ዓመት ማለትም በ2016/17 ሲሆን በዚህ ወቅት ኢንዱስትሪው በአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠኑ (GDP) ላይ ያለው ድርሻ ከ 17% ወደ 25% በማደግ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ አምጥቷል (በዚህ ወቅት የግብርናው እና የአገልግሎት ዘርፎች ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ጋር ሲነጻጸሩ ማሽቆልቆልን አሳይተዋል)፡፡ በዚህ ዓመት ኢንዱስትሪው በአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠኑ (GDP) ላይ ያለው ድርሻ ያሳየው ጭማሬ በአገሪቱ ካለው ለውጥ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፤ በተለይም በብዙ ቦታዎች ያሉት የኢንዱስትሪ ፓርኮች በመጠናቀቃቸው ወይም በ 2016/17 የሚጠናቀቁም በመኖራቸው (ለምሳሌ የኮምቦልቻ እና የመቐሌ ኢንዱስትሪ ፓርኮች) ምክንያት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የኢኮኖሚ ሽግግርን ከማካሄድ አንጻር የኢትዮጲያ መንግሥት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ያደረገው ትኩረት ለውጥን እያመጣ ይመስላል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚቀረውና በቀጣይ ዓመታት መታየት የሚኖርበት ይህ ለውጥ በምን ያህል ደረጃ እንደሚቀጥል ወይም ጭማሬን እንደሚያሳይ ነው፡፡ የተለየዩ ዘርፎች በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸውን ድርሻ የሚመለከተውና ሰፊው የኢኮኖሚ ክፍል የረጅም ጊዜ መረጋጋትን እንደሚያሳይ ጠቋሚ ግኝቶች አሁን ይስተዋላሉ፤ በተለይም በቀጣይ ዓመታት ኢንዱስትሪው የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችልም ይጠበቃል፡፡

ሁለተኛው የምንገመግመው ትርክት ደግሞ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትን በተመለከተ ነው፡፡ ምንም እንኳን የኢትዮጲያ መንግሥት እና የዓለም ባንክ በሚያቀርቡት መረጃዎች መካከል ልዩነት ቢኖርም ከሁለቱም የሚገኙት የመረጃ ስብስቦች እንደሚያሳዩት ኢትዮጲያ

ከአፍሪካ ብሎም ከዓለም በከፍተኛ ደረጃ ከሚያድጉት አገራት መካከል አንዷ እንደሆነችና ይህ ደግሞ ከ2003 ጀምሮ እንደቀጠለ መሆኑን ያሳያሉ (ምስል 2 እና ሠንጠረዥ 2 ተመልከቱ)፡፡ ይህ እድገት አንጻራዊ የመነሻ ነጥብ አለው፤ ምክንያቱም ኢትዮጲያ በዓለም በጣም ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ አጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) ካላቸው አገሮች አንዷ የነበረች ሲሆን አሁንም ከፍተኛ እድገት አስመዝግባም ከዓለም ዝቅተኛ ከሚባሉት ተርታ ትገኛለች፡፡ የኢኮኖሚ እድገት ከመነሻው ካለው የኢኮኖሚ ስፋት ጋር ተነጻጻሪ ስለሆነ ይህ አጽንኦት ያስፈልገዋል፡፡ ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚያስፈልገው ጉዳይ ምንም እንኳን መረጃዎች ፖለቲካዊ ጥቅም እንዲያስገኙ ለውጥ እንደሚደረግባቸውና ከፍ እንደሚደረጉ ቢጠበቅም የኢትዮጲያ መንግሥት የሚያቀርበው የእድገት መጠን የዓለም ባንክ ከሚያቀርበው ሁልጊዜ ከፍተኛ አይደለም፡፡ እንደ Mandefro and Jerven (2015, p. 1) ያሉ ተመራማሪዎች የሦስተኛ ወገን ምንጮችን በማመሳከር እነዚህ ምንጮች የኢትዮጲያን እድገት በተመለከተ "ወጥ በሆነ መልኩ አነስተኛ አጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP)" እንደሚዘግቡ ቢሞግቱም ይህ አስተያየታቸው ከትክክለኛው መረጃ ጋር ሲነጻጸር ተቃርኖ አለው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን በረጅም የጊዜ ሂደት ውስጥ ስንፈትሽ የሚገኘው ትርክት ግን ውስብስብ ሲሆን ይህ ደግሞ የኢትዮጲያ መንግሥት የሚያቀርበው የእድገት መጠን በወጥነት ከፍተኛ እንዳልሆነም ያሳያል፡፡ በምስል 2 እንደሚታየው ባለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ከተመዘገቡት የእድገት መጠኖች ውስጥ በአስሩ የዓለም ባንክ የዘገበው የኢትዮጲያ መንግሥት ከዘገበው ብልጫ አለው፡፡ የኢትዮጲያ መንግሥት የአገሪቱን የእድገት መጠን ከፍ አድርጎ እንደሚያቀርብ ለማሳየት Mandefro (2016) የሁለት ዓመታት የIMF መረጃን እንደ ዋቢ አድርጎ ያቀርባል፤ በተጨማሪም የዓለም ባንክ ዘገባ ከኢትዮጲያ መንግሥት የሚያንስባቸውንም አመታት በማስረጃነት ያቀርባል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዓመታት አጠቃላዩን ሂደት የሚወክሉ አይደሉም፡፡ በቅርብ ዓመታት ግን (ከ2013/14 ጀምሮ) የኢትዮጲያ መንግሥት የሚዘግበው የእድገት መጠን ከዓለም ባንክ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ መሆኑን ግን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡




**ምስል 1.** ዘርፎች በኢኮኖሚው ላይ ያለቸው ድርሻ፤ ከ 1999 እስከ 2018። ምንጭ፡- NBE 2005, 2006, 2007, 2008, 2009, 2010, 2011, 2012, 2013, 2014, 2015, 2016, 2017። ማስታወሻ፡- ዘርፎቹ በኢኮኖሚው ላይ ያላቸውን ድርሻ የሚያሳየው መረጃ ችግር ስላለበትና ወጥነት ስለሚጎድለው አኃዞቹን በሠንጠረዥ ውስጥ አላካተትንም። በተለያዩ ሪፖርቶች ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ አኃዞች በመኖራቸው ምክንያት ትክክለኛ ለመሆናቸው እርግጠኛ አይደለንም (የስልት ክፍሉን ይመልከቱ)። በምትኩ አባሪ የሆነ የመረጃ ሠንጠረዥ ሳናካትት ምስል 1ን ብቻ እናቀርባለን፤ ይህ ደግሞ በሰፊ ደረጃ ያለው ሂደት ላይ የሚያተኩር ነው። ሌሎች ጥናቶች የብሔራዊ ባንክ ዓመታዊ ሪፖርቶች ላይ የሚገኙትን መረጃዎች በድጋሚ በማስላት ዘርፎቹ በኢኮኖሚው ላይ ያላቸውን ድርሻ ማጣራት ይችላሉ።




**ምስል 2.** የኢኮኖሚ እድገት መጠን እና የኢኮኖሚው ስፋት፤ ምንጭ፡- NBE 2005, 2006, 2007, 2008, 2009,2010, 2011, 2012, 2013, 2014, 2015, 2016, 2017; World Bank, 2018፡፡ ማስታወሻ፡- የWorld Bank (2018) መረጃ በጎርጎሮሳውያን ዘመን አቆጣጠር ሲሆን የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ደግሞ የኢትዮጲያን ዘመን አቆጣጠር ይጠቀማል፡፡ በኢትዮጲያ ዘመን አቆጣጠር የሚሸፈነውን የኋለኛውን ዓመት ተጠቅመናል (ይህ ማለት ከ 2004/05 ውስጥ 2005 ወስደናል ምክንያቱም አብዛኛው ጊዜ የሚሸፈነው በዚህ ዓመት በመሆኑ ነው)፡፡ በዚህ ልዩነት ምክንያት ሁለቱ ምስሎች በቀጥታ መነጻጸር አይችሉም፡፡ በመሆኑም በዚህ ልዩነት ምክንያት ቀጥተኛ ንጽጽር በሚደረግበት ወቅት ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡

**ሠንጠረዥ 2.** የኢኮኖሚ የእድገት መጠን (%) እና የኢኮኖሚ ስፋት (በ አሜሪካ ዶላር)

| | Growth Rate (GoE) | Growth Rate (WB) | GDP, Billions (WB) |
|---|---|---|---|
| 99/00 | 5.4 | 6.1 | 8.2 |
| 00/01 | 7.4 | 8.3 | 8.2 |
| 01/02 | –0.3 | 1.5 | 7.9 |
| 02/03 | –3.3 | –2.2 | 8.6 |
| 03/04 | 11.1 | 13.6 | 10.1 |
| 04/05 | 8.8 | 11.8 | 12.4 |
| 05/06 | 9.6 | 10.8 | 15.3 |
| 06/07 | 11.4 | 11.5 | 19.7 |
| 07/08 | 11.6 | 10.8 | 27.1 |
| 08/09 | 9.9 | 8.8 | 32.4 |
| 09/10 | 10.4 | 12.6 | 29.9 |
| 10/11 | 11.4 | 11.2 | 32 |
| 11/12 | 8.8 | 8.7 | 43.3 |
| 12/13 | 9.7 | 10.6 | 47.7 |
| 13/14 | 10.3 | 10.3 | 55.6 |
| 14/15 | 10.2 | 10 | 64.5 |
| 15/16 | 8 | 7.6 | 73 |
| 16/17 | 10.9 | 10.3 | 80.6 |

**ምንጭ፡-** NBE 2005, 2006, 2007, 2008, 2009, 2010, 2011, 2012, 2013, 2014, 2015, 2016, 2017; World Bank, 2018፡፡ ማስታወሻ፡- ከምንዛሬ ለውጥ ጋር በተገናኘ ውስብስብ ጉዳዮች በመኖራቸው ምክንያት አጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) በተመለከተ በ ወቅቱ ባለው የአሜሪካ ዶላር መሰረት የተሰላውን የWorld Bank (2018) መረጃን ተጠቅመናል፡፡ የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክም አጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) ሲዘግብ የሚጠቀመው በወቅታዊ መሠረታዊ ዋጋ ቢሆንም ዝርዝሩ የተቀመጠው በብር ነው፡፡ በዚህ የጊዜ ሰሌዳ በአንድ የበጀት ዓመት እንኳ የተደረጉ ከፍተኛ የገንዘብ ዋጋ ቅነሳዎችን ጨምሮ ላቅ ያለ የገንዘብ መዋዠቅ ነበረ፡፡ ዓላማችን በጊዜ ሂደት ውስጥ ያለውን ሁኔታ መመልከት በመሆኑ ከ ኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ሪፖርቶች የተገኙትን አጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP) አኃዞች በድጋሚ አላሰላናቸውም፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የምንገመግመው ትርክት ግብርና የኢትዮጲያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት እንደሆነ እና ለአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠን (GDP)፣ ለሥራ እድል፣ እና ለውጪ ንግድ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ (ለምሳሌ፡- Cochrane 2017; Haylemariam 2017; Loening et al. 2009) የሚነገረውን ነው፡፡ ይህንን ትርክት ለመመርመር የምንጠቀመው ከኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ የተገኘውን የውጪ እና ገቢ ንግድ መረጃን እና ይህንንም ከሌሎች መረጃዎች ጋር በማነጻጸር ነው፡፡ የግብርና ምርቶች የኢትዮጲያን ኢኮኖሚ እና የውጪ ንግድ ገበያ መቆጣጠራቸው እርግጥ ነው፤ ከእነዚህ ለውጪ ንግድ ከሚውሉት ምርቶች መካከል የቡና ምርት የሚጫወተው ሚና ወሳኝ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ መሰረት ከ አስራ ሁለቱ ቁልፍ የውጪ ንግድ ምርቶች ስድስቱ የግብርና ምርቶች ናቸው (ቡና፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬ፣ አበባ፣ የቅባት እህሎች፣ እና ጫት)፡፡ ከኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ከእነዚህ ስድስት ምርቶች በውጪ ንግድ የሚገኘው ዋጋ ከ 60% በፍጹም ቀንሶ እንደማያውቁ ነው (ምስል 3)፡፡ የቀንደ ከብቶችና ከእነዚህ ጋር ግንኙነት ያላቸው ምርቶች በኢትዮጲያ የውጪ ንግድ ገበያ ውስጥ የሚጫወቱት ሚና ብዙም አይተወቅም፤ ነገር ግን ከ አስራ ሁለቱ ዋና የውጪ ንግድ ምርቶች እነዚህ ሦስቱ ናቸው (ቆዳ፣ ሥጋ፣ እና በሕይወት ያሉ እንስሳት)፡፡ በዋጋ ሲተመን ደግሞ የቀንድ ከብት እና ከቀንድ ከብት ጋር ግንኙነት ያላቸው ምርቶች ከውጪ ንግዱ አንድ

አስረኛውን ይይዛሉ፡፡ በ 2002/03 እና 2016/17 መካከል እነዚህ ሁለት የምርት አይነቶች (ግብርና እና የቀንድ ከብት) አንድ ላይ ከአጠቃላይ የወጪ ንግዱ ዋጋ ከ70% ያላነሰ ይዘዋል፡፡

በውጪ ንግድ መረጃው ላይ አዲስ መታየት የጀመሩ አንድአንድ ጉዳዮችን ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ ግብርና እና ከቀንድ ከብት ጋር የተገናኙ ምርቶች ምንም እንኳን በተከታታይ ዓመታት በውጪ ንግዱ ገበያ ላይ ወሳኝ ቢሆኑም አሁን አሁን ብቅ ማለት የጀመሩ አዳዲስ ምርቶችም አሉ፡፡ ለምሳሌ በ2012/13 የኤሌክትሪክ ኃይል እንደ ዋና የውጪ ንግድ ምርት ሆኖ የመጣ ሲሆን በአጠቃላይ የውጪ ንግዱ ምሕዳር ላይ ግን ያለው ተጽእኖ በአንጻራዊነት አሁንም አናሳ ነው፡፡ ነገር ግን በሰፊ ደረጃ እየተገነቡ ካሉት በውሃ ኃይል ከሚሰሩት ግድቦች በመነሳት በሚመጡት ዓመታት ይህ ቁጥር እንደሚጨምርና የኤሌክትሪክ ኃይልም በውጪ ንግዱ ገበያ ላይ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት እንገምታለን (Department of Commerce 2017a)፡፡ በዚህ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ በአጠቃላይ በውጪ ንግድ የተገኘው ዋጋ ከመጨመሩም ባለፈ የኢትዮጲያ የውጪ ንግድ ምርቶች የሚያዳርሱት ቦታዎችም በእጥፍ ጨምረዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው አናሳ የሆኑት የውጪ ንግድ ምርት ዘርፎች (በዋናነት ግብርና እና የቀንድ ከብት) ሰፊ የሆነ የዓለምአቀፍ ገበያ ፍላጎት እንዳላቸው ነው (ERCA 2018)፡፡




**ምስል 3**. ዋናዎቹ የውጪ ንግድ ምርቶች እና ዋጋቸው በ ሚሊዮኖች የአሜሪካ ዶላር፡፡ ምንጭ፡- NBE 2005, 2006, 2007, 2008, 2009, 2010, 2011, 2012, 2013, 2014, 2015, 2016, 2017፡፡ ማስታወሻ፡- በእያንዳንዱ ዓመት ያለውና ከኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ የተገኘው መረጃ ጥቅም ላይ ውሏል፤ የእያንዳንዱ ዓመት ዋጋ ከተካተተ ከዚህም ላይ የአጠቃላዩ ስሌት በመቶኛ ተቀምጧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3**. ዋናዎቹ የውጪ ንግድ ምርቶች እና ዋጋቸው በ ሚሊዮኖች የአሜሪካ ዶላር

| | Coffee | Oilseeds | Pulses | Fruits & Vegetables | Khat | Flowers | Leather | Meat | Live Animals | Gold | Electricity | Other |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 02/03 | 165.3 | 46.1 | 20 | 9.6 | 58 | - | 52.2 | 2.4 | 0.5 | 42.1 | - | 86.7 |
| 03/04 | 223.5 | 82.7 | 22.6 | 12.7 | 88 | 2.3 | 43.6 | 7.7 | 1.9 | 48.7 | - | 69.2 |
| 04/05 | 335.4 | 102.3 | 35.5 | 16.1 | 100 | 7.8 | 63.7 | 14.6 | 12.8 | 52.5 | - | 85 |
| 05/06 | 354.3 | 211.4 | 37 | 13.2 | 89.1 | 21.8 | 75 | 18.5 | 27.6 | 64.7 | - | 87.8 |
| 06/07 | 424.2 | 187.4 | 70.3 | 16.2 | 92.8 | 63.6 | 89.6 | 15.5 | 35.8 | 97 | - | 91.8 |
| 07/08 | 524.5 | 218.8 | 143.6 | 12.8 | 108 | 111.8 | 99.2 | 20.9 | 40.9 | 78.8 | - | 106.3 |
| 08/09 | 375.9 | 356.1 | 90.7 | 12.1 | 139 | 130.7 | 75.3 | 26.6 | 52.7 | 97.8 | - | 91.3 |
| 09/10 | 528.3 | 358.5 | 130.1 | 31.5 | 210 | 170.2 | 56.4 | 34 | 90.7 | 281 | - | 112.5 |
| 10/11 | 841.8 | 326.6 | 137.9 | 31.5 | 238 | 175.3 | 103.8 | 63.3 | 147.9 | 462 | - | 219 |
| 11/12 | 833.1 | 472.3 | 159.7 | 44.9 | 240 | 197 | 109.9 | 78.8 | 207.1 | 602 | - | 207.1 |
| 12/13 | 745.1 | 437.1 | 232.5 | 43.7 | 271 | 186.1 | 120.6 | 74.1 | 166 | 584 | 34.6 | 214.9 |
| 13/14 | 714.4 | 651.9 | 250.7 | 45.9 | 297 | 199.7 | 129.8 | 74.6 | 186.7 | 456 | 45.3 | 247.4 |
| 14/15 | 780.5 | 510.1 | 219.9 | 47.6 | 272 | 203.1 | 131.6 | 92.8 | 148.5 | 319 | 42.8 | 251.4 |
| 15/16 | 722.7 | 477.2 | 232.4 | 53.7 | 263 | 225.3 | 115.3 | 96.4 | 147.8 | 291 | 31.5 | 212.3 |
| 16/17 | 883.2 | 351 | 279.9 | 56.1 | 273 | 218.5 | 114 | 98.7 | 67.6 | 209 | 73.4 | 283.2 |

**ምንጭ፡**- NBE 2005, 2006, 2007, 2008, 2009, 2010, 2011, 2012, 2013, 2014, 2015, 2016, 2017

የኢትዮጲያ ኢኮኖሚ በጊዜ ሂደት እያሳየ ያለውን ለውጥ የገቢ ንግዱ አካሄድም አመላካች ነው፡፡ የ2016/17 የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ዓመታዊ ሪፖርት ሦስት አስርት ዓመታት ወደኋላ በመመለስ በየዓመቱ የነበሩትን 21 ዋና ዋና የገቢ ንግድ ምርቶችን ይዘረዝራል፡፡ የውጪ ንግድ መረጃውን ባቀረብነው መሰረትም ከ 2002/03 እስከ 2016/17 ድረስ ያለውን የዚህንም መረጃ እናቀርባለን (ምስል 4፣ ሠንጠረዥ 4)፡፡ምስሉ እና ሠንጠረዡ በቀላሉ መነበብ እንዲችሉ ይረዳ ዘንድ በአንጻራዊነት ዝቅተኛ የገቢ ንግድ ደረጃ ያላቸውን 10 ሸቀጦች አላካተትናቸውም (እነዚህም መጠጦች፣ ትንባሆ፣ ድፍድፍ ነዳጅ፣ ኬሚካሎች፣ የሕክምና እና የመድኃኒት ነክ እቃዎች፣ ሳሙና እና አብረቅራቂ ንጥረ-ነገር፣ ወረቀት እና ወረቀት ማምረቻ፣ መስታወት እና የመስታወት እቃዎች፣ ጥራጥሬ፣ እና የቴሌኮም እቃዎች)፡፡ በዚህም መሰረት በ ምስል 4 የተካተቱት ዋና የገቢ ንግድ እቃዎች 11 ናቸው (እነዚህም ምግብ እና በሕይወት ያሉ እንስሳት፣ የነዳጅ ምርቶች፣ ማዳበሪያ፣ የኃማ ውጤቶች፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ አልባሳት፣ ብረታ ብረት እና የብረታ ብረት ማምረቻ፣ ማሽኖች እና አውሮፕላኖች፣ አውቶሞቢሎች፣ የኤሌክትሪክ እቃዎች፣ እና ሌሎችም)፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነገር "ጥራጥሬ" በ "ምግብ እና በሕይወት ያሉ እንስሳት" በሚለው ምድብ ውስጥ የተካተተ ሲሆን በተለይም የጥራጥሬ የገቢ ንግድ ጎልቶ የሚታይባቸውና በሁለት ወይም በሦስት እጥፍ የጨመረባቸው ዓመታት ነበሩ፤ እነዚህም 2008/09፣ 2009/10፣ 2011/12፣ እና 2012/13 ሲሆኑ እነዚህም ጊዜያት በአገሪቱ ውስጥ ድርቅ የተስተዋለባቸው ነበሩ፡፡

የገቢ ንግዱ መረጃ የአገር ውስጥ ፍላጎቶችን ለማሟላት አኮኖሚው በዓለም አቀፉ ገበያ ላይ ጥገኛ የሚሆንባቸውን ነገሮች ከመጠቆሙም በተጨማሪ አንዳንድ ግልጽ ተቅርኖዎችንም አመላካች ነው፡፡ ነዳጅ ከውጪ ወደ አገር ውስጥ የሚገባው አንደኛው ሸቀጥ ነው ምክንያቱም ኢትዮጲያ የአገር ውስጥ አቅርቦት የላትም (ወይም እስከአሁን ድረስ ለአቅርቦት የሚሆን በቂ የምርት መጠን የለም)፤ ይህ ደግሞ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ እና የኃማ ውጤቶችን ከማምረት አቅም ጋር ይገናኛል፡፡ አገሪቱ ያላትን ሐብት መጠቀም እንድትችል ከፍተኛ የሆነ አቅም የምትፈልግበት ዘርፍ የማዕድን ቁፋሮ እና ልማት ሲሆን ይህን ማድረግ ቢቻል አገር ውስጥ የሚያስፈልገውን የብረታ ብረት እና ኤሌክትሪክ እቃዎች አቅራቦት ማሟላት በተቻለ ነበር (Department of Commerce 2017b)፡፡ የኢትዮጲያ አየር መንገድ ፈጣን እድገት እና ቀጣይነት ያለው ስኬት የሚያሳየው የፋብሪካ እና የአውሮፕላን እቃዎች ገቢ ንግድ የሚጫወተውን ነው፡፡ መንግሥት ከፍተኛ የሆነ ቀረጥ በመጣል እና አውቶሞቢሎች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ጥረት ቢያደርግም አሁንም ቢሆን የአገር

ውስጥ አቅራቦቱ ከአገር ውጪ በሆኑ ምንጮች ላይ ጥገኛ ነው፤ በዚህ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ የአውቶሞቢሎች የገቢ ንግድም ከአጠቃላዩ በመቶኛ ሲሰላ በአማካኝ ቋሚ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ኢትዮጲያ ምግብ እና በሕይወት ያሉ እንስሳትን ለውጪ ንግድ የምታቀርብ ሲሆን እነዚህ ሁለቱ በአንድ ላይ ከፍተኛ የሆነ የወጪ ንግድ ድርሻ ዋጋ አላቸው፤ በዚህ ረገድ የሚስተዋለውም ተቃርኖ ኢትዮጲያ ከፍተኛ የሆነ የምግብ እና በሕይወት ያሉ እንስሳት ወደ አገር ውስጥ ማስገባቷ ነው፡፡ ለዚህ ተቃርኖ በተወሰነ መልኩ ምላሽ ማግኘት የሚቻለው ተፈላጊ የሸቀጥ አይነቶችን ስንመለከት ነው፤ በዚህም መሰረት እንደ ሩዝ ያሉት አንዳንዶቹ በገቢ ንግድ የሚገዙት የምግብ ምርቶች በዋናነት በአገር ውስጥ የሚመረቱ ወይም ለውጪ ንግድ የሚቀርቡ አይደሉም፡፡ የጥራጥሬ የገቢ ንግድ ግን የሚያመላክተው ነገር ሌላ ነው፤ ይህ የጥራጥሬ የገቢ ንግድ ፍሰትት አጉልቶ የሚያሳየው አገሪቱ ለድርቅ ያላትን ተጋላጭነት እና ለአስቸኳይ የምግብ ድጋፍ የሚሆን ጥራጥሬን አስፈላጊነት ነው፡፡ እነዚህን የገቢ የንግድ መረጃዎች በተመለከተ ሊታወቅ የሚገባው ጉዳይ የገቢ ንግዱ የሚያጠቃልለው በመንግሥት የሚደረገውን ግዥ ብቻ ሳይሆን የግሉንም ዘርፍ ግዢ ያካትታል፤ በተለይም ጥራጥሬን በተመለከተ ድርቅ በሚከሰትባቸው ዓመታት የምግብ ሸቀጦችን በመግዛት የዕርዳታ ሰጪ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅት ማሕበረሰቡንም መረጃ አብሮ ያካተተ ነው (USDA 2016)፡፡ የምግብ እና በሕይወት ያሉ እንስሳትን የገቢ እና ወጪ ንግድ በተመለከተ በጥልቀት ለመረዳትና ምርመራ ለማድረግ ተጨማሪ ጥናቶች ያስፈልጋሉ፡፡ በኢትዮጲያ ውስጥ ዋና ከሚባሉት የሽያጭ ተክሎች አንደኛው ጥጥ እንደመሆኑ የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት የገቢ ንግድ ከፍተኛ እንደማይሆን ይገመታል፤ ነገር ግን መረጃው የሚያሳየው አልባሳት ዋና የገቢ ንግድ ዝርዝር ውስጥ መኖራቸውን ነው፡፡ የፍላጎት መጠን ከአቅርቦት ጋር አለመጣጣም፣ የአገር ውስጥ የማምረት አቅም አናሳ መሆን፣ በንጽጽር ከፍተኛ የማምረት ወጪ መኖር፣ እና በኢትዮጲያ ለጥጥ ምርት የሚውለው የመሬት ስፋት በሂደት ማሽቆልቆሉ ለሁኔታው በምክንያትነት የሚቀርቡት ማሳያዎች ናቸው (USDA 2018)፡፡ የዚህን የግብርና ኢኮኖሚውን ንዑስ ዘርፍ የበለጠ ለመመርመር፣ ለመረዳትና ዘርፉ ያለውን እምቅ አቅም ለማወቅ ተጨማሪ ጥናቶች ይፈልጋል፡፡

የምጣኔ-ሐብት ውስብስብነት ምልከታ ማዕከል (OEC 2018) በአንድ ዓመት ማለትም በ2016 የነበሩትን የገቢ ንግድ ሸቀጦች በዝርዝር ሲያቀርብ በዚህ ዓመት ከአጠቃላይ የገቢ ንግድ ሸቀጦች 10.1% ድርሻ በመያዝ ከፍተኛ የሆነው የተጣራ ነዳጅ ነው፡፡ በምጣኔ-ሐብት ውስብስብነት ምልከታ ማዕከል የ “ማሽኖች” ምድብ (ይህ ምድብ ብዙ ሸቀጦችን ይዟል) ከአጠቃላይ የገቢ ንግድ ውስጥ 27% ድርሻ አለው፡፡ መጓጓዣ (በዋናነት አውሮፕላን፣ ከባድ መኪናዎችና፣ አውቶሞቢሎች) በዚሁ ዓመት ከነበረው የገቢ ንግድ 13% ድርሻ ሲኖረው በ“ማሽን” ምድብ ውስጥ አልተካተተም፡፡ ይህ ምደባ ትንሽ ቢለይም የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ካቀረበው መረጃ ጋር ይጣጣማል፡፡ ምንም እንኳን የመረጃ ጊዜ ሰሌዳው ውሱን ቢሆንም የWorld Bank (2018) መረጃ እንደሚያሳየው በፍጥነት በማደግ ላይ ካለው ኢኮኖሚ ጋር ሲነጻጸር የሸቀጦችና የአገልግሎት ገቢ ንግድ ከአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠኑ (GDP) በመቶኛ ሲሰላ ማሽቆልቆል አሳይቷል፤ ይኸውም በ2011 ከነበረው 32% በ2017 ወደ 23.7% ዝቅ ብሏል፡፡ ይህ አስፈላጊ የሆነ አውድን ይጠቁማል፤ ከላይ ከላይ ሲታይ በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚታየው የገቢ ንግድ መጨመር አሉታዊ አካሄድ ያለው ቢመስልም በሰፊው የኢኮኖሚ እድገት አውድ ውስጥ ስንመለከተው ከከአጠቃላይ አገራዊ የእድገት መጠኑ (GDP) አንጻር የገቢ ንግዱ በመቶኛ ሲሰለ እያሽቆለቆለ ነው፡፡




**ምስል 4**. ዋና ዋና የገቢ ንግድ ሸቀጦች፣ በዋጋ፡፡ ምንጭ፡- NBE 2016, 2017፡፡ ማስታወሻ፡- በ አሜሪካ ዶላር ከተገለጸው የውጪ ንግድ መረጃ በተቃራኒ የገቢ ንግዱ ዋጋ የተዘረዘረው በብር ነው፡፡ አጠቃላይ በጊዜ ሂደት ያለውን ሂደት ለመፈተሽ ይህ ችግር ይፈጥራል ብለን አናስብም፡፡ እንደ ወጪ ንግዱ መረጃ የመቶኛ ስሌቶቹ ቀመር የተሰራው ከዓመታዊ አኃዞቹ ነው፡፡ በ 2016/17 ሪፖርት ላይ የ2014/15 እና 2015/16 የአንዳንድ ሸቀጦች (ምግብ እና በሕይወት ያሉ እንስሳት፣ የነዳጅ ምርቶች፣ ማዳበሪያ፣ እና የጎማ ውጤቶች) መረጃ አልተካተተም፡፡ የ2014/15 መረጃን ያገኘነው ከ2015/16 ሪፖርት ሲሆን ከዚህ ውጪ ያሉት መረጃዎች በአጠቃላይ የተወሰዱት ከ2016/17 ሪፖርት ነው፡፡ የ2015/16 መረጃ በ2015/16 ሪፖርት ላይ ይገኛል ቢሆንም በአባሪው ላይ ስሕተቶች እንዳሉ ብዙ አመላካቾች አሉ (NBE 2016, p. 122)፤ ለምሳሌ የአኃዞች በአሥር እጥፍ መጨመር ወይም መቀነስ፣ ለተለያዩ ሸቀጦች የአንድ አይነት ቁጥሮች መደጋገም፣ እና የሠንጠረዦች መዘበራረቅ፡፡ አንዳንድ ሸቀጦች በትክክል የተዘረዘሩ ይመስላሉ (NBE 2016, p. 123)፤ ነገር ግን በግማሹ የመረጃ ስብስብ ውስጥ ስሕተቶች ስለነበሩ የዚህን ዓመት መረጃ ባዶ ትተነዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.** ዋና ዋና የገቢ ንግድ ሸቀጦች፣ በዋጋ (በሺህ ብር መጠን)

| | Food & Live Animals | Petroleum Products | Fertilizers | Rubber Products | Textiles | Clothing | Metal & Metal Manfc. | Machinery & Aircraft | Road Motor Vehicles | Electrical Materials | Others |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 02/03 | 1,697,566 | 2,463,917 | 462,662 | 376,787 | 599,604 | 478,039 | 1,311,504 | 1,963,002 | 1,817,630 | 1,059,754 | 2,696,596 |
| 03/04 | 1,981,297 | 2,608,285 | 923,523 | 417,410 | 606,295 | 601,949 | 2,012,945 | 2,397,183 | 2,124,501 | 2,447,540 | 4,152,333 |
| 04/05 | 1,566,093 | 5,736,666 | 1,055,294 | 536,827 | 774,285 | 836,015 | 3,476,768 | 4,553,244 | 2,811,972 | 3,062,726 | 4,853,003 |
| 05/06 | 2,139,779 | 7,422,807 | 1,180,768 | 730,113 | 1,065,381 | 1,291,287 | 4,157,675 | 5,305,516 | 4,183,804 | 2,978,793 | 6,366,919 |
| 06/07 | 1,799,700 | 7,524,664 | 933,867 | 838,145 | 808,907 | 1,523,051 | 4,460,322 | 7,036,854 | 6,062,546 | 2,968,701 | 7,829,238 |
| 07/08 | 2,499,134 | 15,076,123 | 2,828,101 | 1,030,557 | 986,145 | 1,198,037 | 7,051,109 | 7,118,469 | 4,279,547 | 4,404,967 | 12,489,774 |
| 08/09 | 7,251,053 | 17,219,182 | 3,008,355 | 1,422,155 | 1,023,983 | 1,124,962 | 7,990,303 | 8,713,241 | 4,859,888 | 5,866,530 | 20,895,905 |
| 09/10 | 7,713,047 | 18,891,592 | 3,221,932 | 2,220,337 | 1,476,236 | 2,433,694 | 11,618,002 | 12,278,627 | 8,503,493 | 7,728,010 | 25,639,499 |
| 10/11 | 3,966,149 | 22,299,884 | 5,665,269 | 2,515,039 | 1,982,717 | 2,430,231 | 10,778,367 | 16,015,252 | 13,180,603 | 7,195,551 | 34,861,069 |
| 11/12 | 12,692,391 | 35,868,583 | 10,503,430 | 3,373,729 | 2,892,344 | 4,218,310 | 19,678,247 | 20,529,023 | 17,831,730 | 8,696,845 | 43,405,637 |
| 12/13 | 11,635,650 | 26,565,255 | 5,332,244 | 4,030,338 | 2,744,224 | 4,449,522 | 21,688,480 | 28,035,377 | 20,493,273 | 11,912,689 | 46,476,571 |
| 13/14 | 9,165,826 | 47,619,870 | 7,808,484 | 5,858,244 | 4,622,749 | 5,442,436 | 29,939,445 | 36,774,861 | 23,820,186 | 22,735,293 | 54,917,318 |
| 14/15 | 13,155,398 | 39,822,539 | 8,641,772 | 5,979,668 | 5,819,130 | 6,802,500 | 45,631,138 | 45,707,264 | 31,471,855 | 43,251,536 | 69,309,407 |
| 15/16 | | | | | | | | | | | |
| 16/17 | 14,830,981 | 37,325,714 | 12,279,084 | 6,708,574 | 5,416,692 | 8,529,700 | 41,572,482 | 56,981,595 | 33,498,960 | 30,086,052 | 78,480,806 |

**ምንጭ፡-** NBE 2016, 2017

ለብዙዎች የስጋት ምክንያት የሆነውና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚሰማው ትርክት አብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት ያለባቸው የብድር መጠን ሲሆን በተለይም አዳዲስ የገንዘብ ወጪ ማድረጊያ መንገዶች ብቅ ማለታቸውን ተከትሎ እና የቻይና ሚና የብዙ ሪፖርቶችም ትኩረት ከመሆኑ አንጻር ነው (AlJazeera 2018; Kpodo 2018; Reuters 2018)፡፡ የብድር ደረጃዋን በተመለከተ ኢትዮጲያ በቅርብ ጊዜ ወደ "ከፍተኛ የብድር ስጋት አደጋ" ደረጃ (Madowo 2018) እንዲሁም ከ "መካከለኛ ስጋት" ደረጃ ወደ "ከፍተኛ ስጋት" ደረጃ ዝቅ ተደርጋለች (Anberbir 2018)፡፡ የብድር ትርክቱ ከእነዚህ የደረጃ ለውጦች ጋር ተያይዞ የኢትዮጲያ ፖለቲከኞችን ትኩረት በመሳቡ ምክንያት የብድር ፖለሲ ለውጦች እንዲመጡ አድርጓል፡፡ በመሰረቱ በ2006 አነስተኛ የነበረው የ2.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የወጪ ብድር በ2016 23.1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በመድረስ ተመንጥቋል (ምስል 5፣ ሠንጠረዥ 5)፤ ይህ ደግሞ በአስር አመት የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ የአስር እጥፍ የውጪ ብድር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም በተለይ ለኢትዮጲያ እየጨመረ የመጣ የብደር መጠን ትርክት እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጡት ስጋቶች ትክክል ናቸው፡፡ ጉዳዩን እየከፋ እንዲሄድ ያደረገው የውጪ ብድር ከፍ ከማለቱ ጋር ተያይዞ እየጨመረ የመጣው የንግድ ኪሳራ ሲሆን በተለይም ከ2014 ጀምሮ የወጪ ንግድ መቀነስ ከገቢ ንግድ መቀነስ ጋር ባለመመጣጠናቸው በመኃከላቸው ያለው ልዩነት እየሰፋ እንዲመጣ አድርጎታል፡፡ እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከተሾመ በኋላ የተወሰኑ ሰፋፊ ተግባራት በመኖራቸው ከውጪ ብድር እና ንግድ ኪሳራ ችግሮች በተጨማሪ መንግሥት አዳዲስ የፋይናንስ ጫናዎችም ሊኖሩበት ይችላል፡፡ ነገር ግን የብድር ትርክቱ ዋና ትኩረት ቻይና ላይ ነው፡፡ የአንድን አገር ትክክለኛ የሆነውን አጠቃላይ የብድር መጠን መረጃ ማግኘት አዳጋች ነው፤ ነገር ግን ከ2000 እስከ 2014 ኢትዮጲያ ከቻይና የ 12 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ብድር አግኝታለች (New Business Ethiopia 2018)፡፡ ይህ የሚያመላክተው ምንም እንኳን ኢትዮጲያ ባለባት አስጊ የብድር ችግር ውስጥ ቻይና ቁልፍ ሚና ቢኖራትም በአሁን ወቅት አገሪቱ ካለባት የብድር ጫና በአማካኝ ግማሹ ከሌሎች አበዳሪዎች የተገኘ ነው፡፡ ቻይናን ተጠያቂ ማድረግ የታሪኩ ግማሽ አካል ነው፡፡




**ምስል 5**. የውጪ ብድር እና የገቢ እና የወጪ ንግድ ልዩነት፡፡ ምንጭ፡- World Bank 2018፡፡ ማስታወሻ፡- የምጣኔ-ሐብት ውስብስብነት ምልከታ ማዕከል (OEC) (2018) የሚያቀርበው መረጃ የተለየ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ያለውን የገቢ/የወጪ ንግድ ሂደትም ከዚህ በተለየ መልኩ ያስቀምጠዋል፡፡ የምጣኔ-ሐብት ውስብስብነት ምልከታ ማዕከል (OEC) የሚጠቀመው በ BACI International Trade Database የተስተካከለውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስታቲስቲክስ ክፍል መረጃን ነው፡፡ የምጣኔ-ሐብት ውስብስብነት ምልከታ ማዕከል (OEC) በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚኖረውን የምንዛሬ ዋጋ ለውጥ እንዴት እንዳስተካከለው ግልጽ አይደለም፤ በተጨማሪም ዋጋው መሰረት የተደረገበትን ዓመት የወሰነበትም አካሄድ ግልጽ አይደለም (ይህ ከተደረገ በዚህ ዓመት ያሉት አኃዞች በዚህ ዓመት ያለውን የምንዛሪ ዋጋ ይይዛሉ)፡፡ የምጣኔ-ሐብት ውስብስብነት ምልከታ ማዕከል (OEC) መረጃዎች ግልጽ ካለመሆናቸው የተነሳ የዓለም ባንክን መረጃ ለመጠቀም መርጠናል፡፡ የዚህ መረጃ ከምጣኔ-ሐብት ውስብስብነት ምልከታ ማዕከል (OEC) መረጃ ጋር በንጽጽር አላቀረብንም ምክንያቱም የመረጃ ስብስቦቹ እንዴት ሊነጻጸሩ እንደሚችሉ ግልጽ ስላልሆነ ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 5**. የውጪ ብድር እና የገቢ እና የወጪ ንግድ ልዩነት፡፡

| | Export Value (2018 US$, 2000 = 100) | Import Value (2018 US$, 2000 = 100) | Debt Stocks (2018 US$ Billions) |
|---|---|---|---|
| 99 | 96.2 | 122 | 5.6 |
| 00 | 100 | 100 | 5.5 |
| 01 | 93.7 | 143.7 | 5.8 |
| 02 | 98.9 | 126.4 | 6.6 |
| 03 | 102.2 | 213.1 | 7.3 |
| 04 | 139.7 | 228 | 6.6 |
| 05 | 186 | 324.9 | 6.2 |
| 06 | 214.8 | 413.1 | 2.3 |
| 07 | 263 | 460.9 | 2.7 |
| 08 | 329.8 | 656.7 | 2.9 |
| 09 | 333.2 | 608.4 | 5.4 |
| 10 | 479.7 | 682.5 | 7.3 |
| 11 | 592.1 | 705.8 | 8.6 |
| 12 | 595.4 | 945.2 | 10.5 |
| 13 | 640.8 | 969.9 | 12.6 |
| 14 | 705.7 | 1233.8 | 16.3 |
| 15 | 628 | 1341.9 | 20.1 |
| 16 | 601 | 1316.1 | 23.1 |

**ምንጭ፡-** World Bank 2018፡፡ ማስታወሻ፡- በሠንጠረዥ 3 እና 5 ያሉት የውጪ ንግድ ዋጋዎች ልዩነት አላቸው፡፡ ለዚህ አንደኛው ምክንያት ሊሆን የሚችለው የዓለም ባንክ በአሁን ወቅት ያለውን የአሜሪካ ዶላር ዋጋ (2018) ስለሚጠቀም የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ዓመታዊ ሪፖርት ግን በእያንዳንዱ ዓመት ያለውን የአሜሪካ ዶላር ዋጋ ስለሚጠቀም ነው፡፡ በሠንጠረዥ 3 ላይ ድምር ዋጋውን አላስቀመጥንም ምክንያቱም በአንድ ቋሚ ዋጋ መሰረት ማስተካከያ ስላልተደረገለት ነው፤ በምትኩ በሠንጠረዥ 5 ላይ የወጪ ንግድን ድምር ዋጋዎች ብቻ አስቀምጠናል፡፡

## 4. ውይይት

የኢትዮጲያን ማክሮ ኢኮኖሚ በተመለከተ ብዙ ትርክቶችና ተቃርኖ-ትርክቶች አሉ (Mandefro 2016)፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ እነዚህ ትርክቶች መሰረት ያደረጉት ነጠላ የመረጃ ነጥቦችን ወይም የተወሰኑ ዓመታትን መረጃ ነው፡፡ ይህ ጽሁፍ ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ ያለን መረጃ በመመርመር በጊዜ ሂደት ያለን ሁኔታ ለማቅረብ እና አራት የተለመዱ ትርክቶች ለመመርመር ሞክሯል፡፡ በዚህ ጽሁፍ የስልት ክፍል እንደተገለጸው እነዚህን ትርክቶች በመመርመር ወቅት ያጋጠመው ዋነኛ ችግር የመረጃ እርስ በእርሱ መጋጨት ወይም ወጥ አለመሆን ነው፡፡ በተለይም ከአንድ መንግሥት ተቋም የተወሰዱ የመረጃ ነጥቦች ከሪፖርት ሪፖርት ልዩነት አላቸው፡፡ ይህ ለጥናቱ ስልታዊ ችግርን ፈጥሯል፤ በዋናነትም የኢኮኖሚውን ነባራዊ ሁኔታ ለመረዳት ችግር ፈጥሯል ምክንያቱም በችግሩ ምክንያት የሚስተዋለው ልዩነት በብር ሲተረጎም በሚሊየኖች የሚቆጠር ነው፡፡ የኢኮኖሚ እድገት ትርክትን ለማስተዋወቅ አንዳንድ አኃዞች ታስቦባቸው እን በዓላማ ለውጥ ተደርጎባቸዋል የሚሉ ግምቶች (እና ክሶች) ይሰማሉ (Mandefro 2016ን ተመልከቱ)፡፡ አንዳንድ

ለውጦች በዚህ መልክ ተደርገው ሊሆን እንደሚችል ተመልክተናል፤ የዚህ ተቃራኒም የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች ተመልክተናል፡፡ እኛም እንደሌሎቹ የምናስተጋባው ጥሪ የብሔራዊ ስታትስቲክስ ተቋማት እና ከቀረጥ፣ ከንግድ፣ ከፋይናንስና መሰል ጉዳዮች ጋር የሚገኙ ሌሎችም ተቋማት አቅም መጎልበት እንዳለበት ነው (Carletto et al. 2015; Jerven 2013; Sandefur and Glassman 2015; Sundaram 2016)፡፡

መጀመሪያ የተመለከትነው ትርክት የኢኮኖሚ ሽግግር ትርክትን ሲሆን ይኸውም የተለያዩ ዘርፎች በጊዜ ሂደት ውስጥ በኢኮኖሚ ላይ ያላቸውን ድርሻ የሚፈትሽ ነው፡፡ የኢትዮጲያ መንግሰት እንደሚያስተዋውቀው በኢኮኖሚው ላይ የግብርናው ዘርፍ ድርሻ በተወሰነ መልኩ እየቀነሰ እንደመጣና የአገልግሎት እና ኢንዱስትሪ ዘርፎች ድርሻ ደግሞ በተወሰነ መልኩ እየጨመረ እንደመጣ ነው፤ የእኛም ግኝት ይህንን ይጠቁማል፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ግኝት ለየት የሚለው በ 2016 ማለትም መረጃ ባገኘንበት የመጨረሻው ዓመት ያለው መረጃ ሲሆን በዚህ ዓመት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከፍተኛ መጨመርን አሳይቷል (ከ 17% ወደ 25%)፡፡ ይህ የተከሰተው ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በተከፈቱበት እና/ወይም ለመከፈት በደረሱበት ወቅት ነው፡፡ ቢሆንም እያንዳንዱ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ድርሻ የሚያሳየው መረጃ ወጥነት የሌለውና በተለየ መልኩ ችግር ያለበት ነው፡፡ የኢንዱስትሪው ዘርፍ እድገት እስካሁን ባሉት ዋና የውጪ ንግድ ሸቀጦች ዝርዝር ላይ አዲስ የጨመረው አየነት የለም፡፡ ነገር ግን የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ሪፖርቶች ታሪክን ስንመለከት ሸቀጦች በውጪ ንግድ ዝርዝር ውስጥ ለመካተት የሚበቁት ለረጅም ዓመታት ከፍተኛ የሆነ የውጪ ንግድ ገቢ ካስገኙ በኋላ ይመስላል፡፡ ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ኃይል እስከ 2014/15 ድረስ በዓመታዊ ሪፖርቶች ውስጥ ሲካተት አንመለከትም፤ ነገር ግን በተካተተበት ዓመት የዚህ አዲስ ሸቀጥ የ 2012/13 እና 2013/14 የውጪ ንግድ መረጃዎችም እብረው ተካተዋል፡፡ በኢንዱስትሪው ዘርፍም ተማሳሳይ ሂደት ሊያጋጥም እንደሚችል እንገምታለን፡፡

ሁለተኛው ትርክት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትን የተመለከተ ሲሆን በተጨማሪም የኢትዮጲያ መንግሥት የእድገቱን አኃዝ ይጨምራል የሚለውንም ክስ የሚመለከት ነው፡፡ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን የኢኮኖሚ እድገት መጠንን በተመለከተ ከኢትዮጲያ መንግሥትም ሆነ ከሦስተኛ ወገን ምንጮች የተገኙት መረጃዎች ከፍተኛ የሆነና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንዳለ ያረጋግጣሉ፡ ፡የእድገቱ ትክክለኛ ባሕሪ እንደየምንጮቹ ልዩነት አለው፡፡ የኢትዮጲያ መንግሥት የእድገት መጠኑን ከፍ በማድረግ ከነባራዊ ሁኔታው የተለየ ብሩሕ የኢኮኖሚ እድገት ምስል እንደሚያቀርብ የሚነሳውን ክስ ለመመልከት እንዲያስችለን የኢትዮጲያ መንግሥት እና የዓለም ባንክ የሚያቀርቡት የእድገት መጠኖች ለማነጻጸር ሞክረናል፡፡ እነዚህ ሁለት የመረጃ ስብስቦች በተለያየ የበጀት ዓመት የዘመን መቁጠሪያዎች በመዘጋጀታቸው ምክንያት በቀጥታ ማነጻጸር አይቻልም፡፡ ነገር ግን የኢትዮጲያ መንግስት ከሦስተኛ ወገኞች ይልቅ በተደጋጋሚ የእድገት መጠን አኃዞችን ከፍ እንደሚያደርግ የሚቀርቡት ክሶች ትክክል እንዳልሆኑ የረጅም ጊዜያትን መረጃዎች በመፈተሽ ተመልክተናል፡፡ በኢትዮጲያ መንግሥት የቀረቡት የእድገት መጠን አኃዞች ከዓለም ባንክ ከፍ የሚሉት በቅርብ ጊዜያት ሲሆን (ከ 2014 እስከ 2017) መረጃ ባገኘንበት ተከታታይ 18 ዓመታት ግን እንዲህ አልነበረም፡፡

ሦስተኛው የተመለከትነው ትርክት የኢትዮጲያ ኢኮኖሚ በዋናነት ግብርና-መር ነው የሚል ሲሆን ይህ ጠቅለል ያለ አስተያየት ግልጽ በሆኑ አኃዞች ተደግፎ አይቀርብም፡፡ ዋጋን በተመለከተ የግብርና ምርቶች በተከታታይ ዓመታት ያለውን የውጪ ንግድ እንደተቆጣጠሩት ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ የግብርናው ዘርፍ አንዳንድ ጊዜ ከሚገለጸው በላይ ወሳኝ ነው፤ ምክንያቱም በተመለከትንበት የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ባለው በየትኛውም ዓመት በውጪ ንግዱ ውስጥ ያለው የግብርና ድርሻ ከ 60% ቀነሶ አያውቅም፡ ፡ በዚህ የጊዜ ሰሌዳ የቀንድ ከብት ጋር የተገናኙ ሸቀጦችን ከጨመርን ሁለቱ ዘርፎች (ግብርና እና የቀንድ ከብት) ከውጪ ንግድ ሸቀጦች በዋጋ ከ70% አያንሱም፡፡ በመሆኑም የኢትዮጲያ ኢኮኖሚ በግብርና ሸቀጦች ላይ እንደሚመሰረት የሚነገረው ትርክት በተለይም የውጪ ንግድ ምርቶችን ከተመለከትን እንዲያውም መጠኑ ከተባለው በላይ ነው፡፡ ከ 2012/13 ጀምሮ በሚስተዋለው የኤሌክትሪክ ኃይል የውጪ ንግድ መጨመር እና ብቅ ማለት በጀመረው የኢንዱስትሪው ዘርፍ ምክንያት በመጪው ዓመታት የውጪ ንግድ ገበያው በአይነቱ ሊሰፋ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የዚህ ለውጥ የስፋት መጠን ገና ወደፊት የሚታይ ነው፡፡ በቅርብ እና በመካከለኛ ጊዜያት የኢትዮጲያ ዋና ዋና የውጪ ንግድ ሸቀጦች ከግብርና ዘርፉ የተገኙ መሆናቸውን ይቀጥላሉ፡፡ የኢትዮጲያ መንግሥትም ይህንን

በአግባቡ በመገንዘብ ልማቱን የሚወስነው የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሆነ ያሳስባል (NPC 2016)፡፡ በዚህ ጸሁፍ ውስጥ በኢኮኖሚው ሽግግር ወቀት ስለሚኖረው የጥቅም ክፍፍል ጉዳዮች አልተመለከትንም፡፡ በእድገት እና ምርታማነት ላይ የሚደረግ ትኩረት አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል የሚገኝበትንና በትንንሽ አርሻ የሚተዳደሩ ገበሬዎችን ከመደገፍ ወይም ከፍተኛ የምርታማነት አቅም ካላቸው አካባቢዎች ውጪ የሚኖረው የማሕበረሰብ ክፍልን ከመደገፍ ጋር እኩል እንዳልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድ ያስፈልጋል (Cochrane 2017)፡፡ እንዲያውም ይህ አይነት እድገት የሚመጣው እነሱን ጉዳት ላይ ጥሎ ሊሆን ይችላል፡፡ የገቢ ንግዱ መረጃ አኮኖሚውን ጠለቅ ብለን እንድናውቅ ከማገዙም ባለፈ በተለይም በድርቅ ጊዜያት የግብርናው ዘርፍ በተደጋጋሚ የአገር ውስጥ ፍላጎትን ማሟላት አለመቻሉን በማሳየት የዘርፉን ተጋላጭነት ያመላክተናል፡፡

አራተኛው ትርከት መሰማት የጀመረው በቅርቡ ሲሆን ይኸውም የአፍሪካ አገራት በከፍተኛ የብድር ጫና ውስጥ እንደሆኑና በተለይም የቻይናን ሚና እና አስቸጋሪ አበዳሪ የመሆኗን ጉዳይ የሚያጎላ ነው፡፡ የብድር ጫናው ትርክት በመረጃ የተደገፈ ሲሆን የኢትዮጲያም የብድር መጠን በአስር ዓመት ውስጥ ብቻ በአስር እጥፍ ጨምሯል፤ በዚህም የከፍተኛ የብድር መጠን ስጋት እና የብድር ጫናው በኢኮኖሚው ላይ የሚፈጥረውን ውጥረት በመመልከት አንዳንድ አበዳሪ ተቋማት የኢትዮጲያ መንግሥትን ደረጃ ዝቅ አድርገውታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የገቢ እና ወጪ ንግድ ኪሳራ መጨመር አንድ ላይ በመደመር የኢኮኖሚ ችግሩን ይበልጥ ሊያከፉት እንደሚችሉ ጠቃሚ ነው፡፡ በ2018 ሊደረጉ ያሉ ለውጦችንም ታሳቢ በማድረግ የብድር ችግሩ እንደሚባባስ እናስባለን፡፡ የኢትዮጲያን የብድር ችግር በተመለከተ የቻይናን ሚና ነጥሎ ማውጣት ግን የታሪኩ ግማሽ አካል ብቻ ነው፡፡ ያለው መረጃ እንደሚጠቁመው ቻይና ከፍተኛዋ የኢትዮጲያ አበዳሪ መሆኗን ነው፡፡ ነገር ግን ብዛት ያላቸው ሌሎች አበዳሪዎችም አሁን ላለው የብድር መጠን አስተዋጽኦ ሲኖራቸው ከቻይና ውጪ ያሉት ሌሎች አበዳሪዎች በአማካኝ ግማሹ የብድር ጫና ፈጣሪዎች ናቸው፡፡

## 5. መደምደሚያ

ይህ ጽሁፍ የረጅም ጊዜ መረጃዎችን በመጠቀም የኢትዮጲያን ማክሮ ኢኮኖሚ የሚመለከቱና የተለመዱ አራት ትርክቶችን ፈተሿል፡፡ አንዳንድ ጉዳዮችን ስንመለከት ትርክቶቹ በተገኙት መረጃዎች ድጋፍ የላቸውም፣ አንዳንዶቹ መረጃዎች ደግሞ ጎዶሎ ሲሆኑ አንዳንድ ጉዳዮችን ስንመለከት ደግሞ ገዥ የሆኑት ትርክቶች ትክክል ናቸው፡፡ እነዚህን ትርክቶች በመመርመር ሂደት ውስጥ ያስተዋልነው አንደኛው ጉዳይ እኛን ጨምሮ ብዙ ተመራማሪዎች የትርክቶቹን እውነተኝነት ለማረጋገጥ በሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች፣ በነጠላ የመረጃ ነጥቦች፣ እና በተወሰኑ ዓመታት መረጃዎች ላይ መሰረት ማድረጋችንን ነው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ግኝቶችም መሰረት እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ምንም እንኳን መረጃዎች በዳኞች በተገመገሙ የጥናት ጽሁፎች ወይም ከፍተኛ ከበሬታን ባገኙ አለም አቀፍ ተቋማት በሚያሳትሟቸው ሪፖርቶች ውስጥ ቢገኙም እንኳን ተመራማሪዎች ወደ መጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች በተደጋጋሚ እንዲመለሱ ጥሪ እናቀርባለን፡፡ ይህንን ማድረግ የራሳችንን መላምቶች በተደጋጋሚ እንድንፈትሽ ከማገዙም በላይ በረጅም ጊዜ ውስጥ ሂደቶች ወጥ መሆናቸውን ወይም በቅርብ በመጡ ለውጦች ምክንያት ማስተካከያ ያስፈልግ እንደሆነ እንድንመለከት ያግዙናል፡፡ የተሻለ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ላይ ሐብትን ማዋል፣ የመረጃ ምርመራን ማሻሻል እና፣ በጥናቶች ጥቅም ላይ የሚውሉት ስልቶች አስተማማኝ እና ከጥናቶች ዓላማ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ጉዳዮች እንደሆኑ ብዙዎች አሳስበዋል (ለምሳሌ፡- Carletto et al. 2015; Jerven 2013; Sandefur and Glassman 2015; Sundaram 2016)፡፡ ሁሉም ነገሮች መልካም ሆነው ከቀጠሉ እነዚህ ለውጦች ከመካከለኛ ጊዜ እስከ ረጅም ጊዜ ውስጥ ይሳካሉ፡፡ እነዚህ ለውጦች እስከሚመጡ ድረስ ግን አሁን ያለው መረጃ የወጥነት ችግር እንዳለው በማግኘታችን ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ጥልቅ የሆነ ፍተሻ ሊደረግበት ያስፈልጋል፡፡ አንባቢዎች ያለውን የወጥነት ችግር በመገንዘብና ይህንንም መረጃም በማግኘታቸው ምክንያት መረጃዎች ለፖለቲካ ጥቅም የመዋል አቅም እንዳላቸውም ሊገነዘቡ ይገባል፡፡

**የጸሐፊዎች አስተዋጽኦ፡** ሎገን ኮክረን የመጻፍና የምርመራውን ሂደት መርቷል፣ የሺጥላ ወ. በቀለ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ይህ ጥናት የተዘጋጀው በሁሉም ጸሐፊዎች ነው፡፡

**ድጋፍ፡** ይህ ጥናት ምንም አይነት የውጪ ድጋፍ አልተደረገለትም

**የጥቅም ግጭት፡** ጸሐፊዎቹ ምንም አይነት የጥቅም ግጭት እንደሌለ ያረጋግጣሉ

**ዋቢ**


ABP. 2017. List of Industrial Zones in Ethiopia. Available online: https://africabusinesspartners.com/perspectives/business/list_of_industrial_zone_in_ethiopia.html (accessed on 8 September 2018).

Allaro, Hailegiorgis Biramo. 2012. The Effect of Export-Led Growth Strategy on the Ethiopian Economy. American Journal of Economics 2: 50–56.

AlJazeera. 2018. At China-Africa Summit, Officials Dismiss Debt Criticism. Available online: www.aljazeera.com/news/2018/09/china-summit-african-leaders-dismiss-debt-criticism 180904145150751.html (accessed on 8 September 2018).

Anberbir, Yohannes. 2018. House Awakens to Country's Debt Stress. Available online: www.thereporterethiopia.com/article/house-awakens-countrys-debt-stress (accessed on 8 September 2018).

Carletto, Calogero, Dean Jolliffe, and Raka Banerjee. 2015. From Tragedy to Renaissance: Improving Agricultural Data for Better Politics. Journal of Development Studies 51: 133–48.

Clapham, Christopher. 2017. The Ethiopian Developmental State. Third World Quarterly 39: 1151–65.

Cochrane, Logan. 2017. Strengthening Food Security in Rural Ethiopia. Ph.D. Thesis, University of British Columbia, Kelowna, BC, Canada.

Cochrane, Logan, and Yeshtila W. Bekele. 2018. Average Crop Yield (2001–2017) in Ethiopia: Trends at National, Regional and Zonal Levels. Data in Brief 16: 1025–33.

Cochrane, Logan, and Nitya Rao. 2018. Is the Push for Gender Sensitive Research Advancing the SDG Agenda of Leaving No One Behind? Forum for Development Studies, doi:10.1080/08039410.2018.1427623

Cowen, Tyler. 2018. Ethiopia Already Is the 'China of Africa'. Available online: www.bloomberg.com/view/articles/2018-05-29/ethiopia-already-is-the-china-of-africa(accessed on 8 September 2018).

Dejene, Melisew, and Logan Cochrane. 2018. Ethiopia's Developmental State: A Building Stability Framework Assessment. Development Policy Review, doi:10.1111/dpr.12414.

Department of Commerce. 2017a. Ethiopia—Energy. Available online: https://www.export.gov/article?id=Ethiopia-Energy (accessed on 8 September 2018).

Department of Commerce. 2017b. Ethiopia—Mining Industry. Available online: https://www.export.gov/article?id=Ethiopia-Mining-Industry(accessed on 8 September 2018).

ERCA. 2018. Import and Export Data of Ethiopia. Available online: http://www.erca.gov.et/index.php/component/hscode/?view=importexport&iccaldate=2014-5-1

Geda, Alemayehu. 2011. Readings on the Ethiopian Economy. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Haylemariam, Dawit Ayele. 2017. How Real is the Ethiopia Rising Narrative? Available online: https://www.huffingtonpost.com/dawit-ayele-haylemariam/how-real-is-the-ethiopia-_b_7985180.html (accessed on 8 September 2018).

IMF. 2013. The Federal Democratic Republic of Ethiopia, 2013 Article IV Consultation. IMF Country Report No. 13/308. Washington: International Monetary Fund.

Jerven, Morten. 2013. Poor Numbers: How We Are Misled by African Development Statistics and What We Can Do about It. Ithaca: Cornell University Press.

Kopf, Dan. 2017. The Story of Ethiopia's Incredible Economic Rise. Available online: https://qz.com/africa/1109739/ethiopia-is-one-of-the-fastest-growing-economies-in-the-world/ (accessed on 8 September 2018).

Kpodo, Kwasi. 2018. IMF Warns of Rising African Debt Despite Faster Economic Growth. Available online: https://www.reuters.com/article/us-africa-imf/imf-warns-of-rising-african-debt-despite-faster-economicgrowth- idUSKBN1I9114 (accessed on 8 September 2018).

Loening, Josef L., Dick Durevall, and Yohannes A. Birru. 2009. Inflation Dynamics and Food Prices in an Agricultural Economy: The Case of Ethiopia. Working Paper in Economics No 347. Gothenburg: Goteborgs Universitet.

Madowo, Larry. 2018. Should Africa be Wary of Chinese Debt? Available online: https://www.bbc.com/news/world-africa-45368092 (accessed on 8 September 2018).

Mandefro, Hone. 2016. Politics by Numbers: Poverty Reduction Discourse, Contestations and Regime Legitimacy in Ethiopia. International Review of Sociology 26: 386–406.

Mandefro, Hone, and Morten Jerven. 2015. GDP Growth and Poverty Decline in Ethiopia: Who Owns the Numbers? Available online: http://addisstandard.com/gdp-growth-and-poverty-decline-in-ethiopia-whoowns-the-numbers/ (accessed on 8 September 2018).

Menyah, Kojo, and Yemane Wolde-Rufael. 2013. Government Expenditure and Economic Growth: The Ethiopian Experience, 1950–2007. Journal of Developing Areas 47: 263–80.

MoFED. 2014. Growth and Transformation Plan Annual Progress Report for F.Y. 2012/13. Addis Ababa: Ministry of Finance and Economic Development.

MoFED. 2017. A Note on Development of FDI in Ethiopia. Fiscal Report Series No 001/2017. Addis Ababa: Ministry of Finance and Economic Development.

NPC. 2016. Growth and Transformation Plan (GTP) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (2015/16–2019-20). Addis Ababa: National Planning Commission.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2005. Annual Report 2004/05. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2006. Annual Report 2005/06. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2007. Annual Report 2006/07. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2008. Annual Report 2007/08. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2009. Annual Report 2008/09. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2010. Annual Report 2009/10. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2011. Annual Report 2010/11. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2012. Annual Report 2011/12. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2013. Annual Report 2012/13. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2014. Annual Report 2013/14. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2015. Annual Report 2014/15. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2016. Annual Report 2015/16. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

NBE [National Bank of Ethiopia]. 2017. Annual Report 2016/17. Addis Ababa: National Bank of Ethiopia.

New Business Ethiopia. 2018. The Government of China has Agreed to Extend Debt Settlement Period for Ethiopia, Premier of Ethiopia Said. Available online: http://newbusinessethiopia.com/china-extendsethiopias-debt-settlement-period/ (accessed on 8 September 2018).

OEC. 2018. Ethiopia. Available online: https://atlas.media.mit.edu/en/profile/country/eth/#Imports (accessed on 8 September 2018).

Rammelt, Crelis F., Maarten van Schi, Fredu Nega Tegabu, and Maggi Leung. 2017. Vaguely Right or Exactly Wrong: Measuring (Spatial) Distribution of Land Resources, Income and Wealth in Rural Ethiopia. Sustainability 9: 962.

Reuters. 2018. China Says Projects Not to Blame for Majority of Africa Debt. Available online: https://www.reuters.com/article/us-china-africa/china-says-projects-not-to-blame-for-majority-of-africadebt-idUSKCN1LD0UT (accessed on 8 September 2018).

Sandefur, Justin, and Amanda Glassman. 2015. The Political Economy of Bad Data: Evidence from African Survey & Administrative Statistics. Journal of Development Studies 51: 116–32.

Sundaram, Jomo Kwame. 2016. The MDGs and Poverty Reduction. In Poverty and the Millennium Development Goals. Edited by Alberto Cimadamore, Gabriele Koehler and Thomas Pogge. London: Zed Books, pp. 26–44.

UNDP. 2015. Inclusive Growth and Inequalities in the Context of Structural Transformation: Ethiopia. Issue Brief. Available online: http://www.et.undp.org/content/dam/ethiopia/docs/Updated%20Final%20%20Inequality%20issues%20brief-1.pdf (accessed on 8 September 2018).

USDA. 2016. Drought Pushes Ethiopia's Wheat Imports to a Record 2.5 MMT. GAIN Report No ET1603. Washington: USDA Foreign Agricultural Service.

USDA. 2018. Ethiopia's Cotton Production Down—Imports Likely Up. GAIN Report No ET1801. Washington: USDA Foreign Agricultural Service.

World Bank. 2018. Ethiopia. Available online: https://data.worldbank.org/country/ethiopia (accessed on 8 September 2018).

Zenawi, Meles. 2012. States and Markets: Neoliberal Limitations and he Case for a Developmental State. In Good Growth and Governance in Africa: Rethinking Development Strategies. Edited by Akbar Noman, Kwesi Botchwey and Howard Stein. New York: Oxford University Press, pp. 140–74.

Zenawi, Meles. n.d. African Development: Dead Ends and New Beginnings. Preliminary draft.

© 2018 by the authors. Licensee MDPI, Basel, Switzerland. This article is an open access article distributed under the terms and conditions of the Creative Commons Attribution (CC BY) license (http://creativecommons.org/licenses/by/4.0/).